# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኤምባሲ
## ለንደን

# Embassy of the Federal Democratic Republic of Ethiopia
## LONDON


ቀን፡ ጥቅምት 16 ቀን 2013 ዓ.ም

ቁጥር፡ ኢ.ኤም.ለ. 135/4/11/2013

በዩናይትድ ኪንግደምና ሰሜን አየርላንድ ለምትገኙ የኢትዮጵያ ዳያስፖራ አባላት

<u>ለንደን</u>

ለአገራችን የከተማ የቱሪዝም ዘርፍ ዕድገት ከፍተኛውን አስተዋጽኦ የሚጫወቱ የአዲስ አበባ ወንዞች ዳርቻ ልማት ፕሮጀክቶች አካል የሆኑት የታላቁ ቤተመንግስት አንድነት ፓርክ ፕሮጀክት፣ የእንጦጦ ፓርክ እና የኢትዮ ቻይና ትብብር ፓርክ በ'ገበታ ለሸገር' የሃብት ማሰባሰብ ሂደት ከህዝብ እና ከልማት አጋሮች በተገኘ ሃብት በአጭር ጊዜ በስኬታማ ሁኔታ ተጠናቀው ለጎብኚዎች ክፍት መደረጋቸው ይታወሳል፡፡

እነዚህን ፕሮጀክቶች በተለያዩ የአገሪቱ አከባቢዎች በማስፋፋት በዘርፉ ሁለንተናዊ ለውጥ ለማምጣት በታቀደው መሰረት በመጀመሪያው ምዕራፍ በኮይሻ፣ በወንጪ እና በጎርጎራ የቱሪስት መዳረሻዎችን ለማልማት ለተጀመረው እንቅስቃሴ በተለያዩ አገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን፣ ትውልድ ኢትዮጵያውያን እንዲሁም የኢትዮጵያ ወዳጆች የፋይናንስ ድጋፍ እንዲያደርጉ መንግስት ጥሪ አቅርቧል፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ በቀጣዮቹ በ2 ሳምንታት ውስጥ ለሚካሄደው የገቢ ማሰባሰብ ፕሮግራም መሠረት ኤምባሲያችን እ.ኤ.አ. ከመጪው ረቡዕ አክቶበር 28 ቀን እስከ እሁድ ኖቬምበር 1 ቀን 2020 በማህበራዊ ሚዲያዎቹ የገቢ ማሰባሰብ ዘመቻ ያካሂዳል፡፡ በመሆኑም ሁላችሁም የዚሁ ዘመቻ አካል በመሆን የበኩላችሁን እንድትለግሱ መልካም ትብብራችሁን እየጠየቅን ቀጥሎ የተጠቀሰውን የባንክ አካውንት በመጠቀም ወይም በአካል በኤምባሲው በመገኘት የገንዘብ ድጋፉን ማድረግ የሚቻል መሆኑን በትህትና እንገልጻለን፡፡

Account Name: Embassy of Ethiopia,
Bank Name : Lloyds
Account No.: 43178968
Sort Code: 306541
Reference: Gebeta

ከሠላምታ ጋር

ተፈሪ መለሰ ደስታ

አምባሳደር


17 PRINCES GATE
LONDON, SW7 1PZ
www.ethioembassy.org.uk

TEL: 020 7589 7212
FAX: 020 7584 7054
e-mail: info@ethioembassy.org.uk